# በርጩማማ ሞቷል!

ከዓሣዬ

የበርጩማ እሬሣን ፣ እንደ እርኩሥ ፈርጆት
ፍትሃት እንዳይደረግ ፣ ተዝካር ላይወጣለት
ይግባኝ በማይሉት ፣ በሰበር ተፈርዶበት፣
በርጩማማ ሞቷል ፣ በደንብ ላሥተዋለ
በሥልጣን ፣ በጥቅም ፣ ልቡ ካልታወረ፣
አዎ!
ዳግም ላይነሣ ፣ ሞቶ ከተቀበረ
ይኸው ሁለት ወራት ፣ ከግማሽ አሥቆጠረ!።

ከበደ ሚካኤል ፣ በአንዱ መጽሃፋቸው
እንዲህ ብለው ነበር ፣ በዝነኛ ብዕራቸው፣
ቆዳ ሻጭ ነጋዴን ፣ ነጋድራሱ ጠርቶ
አምጣ አለው ቆዳውን ፣ ሊገዛው ተሥማምቶ፣
ኋላም ነጋድራሱ ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ
ቆዳው ይገማል አለው ፣ በጣም ተጠይፎ፣
ሥግብግቡም ነጋዴ ፣ እምቢኝ እንዳይለው
ከቆዳው እኮ ሣይሆን ፣ ጌታዬ ግማቱ ከኔ ነው
ብሎ ጫማ  ሥሞ ፣ አጥብቆ  ቢለምነው፣
አፍንጫውን ይዞ ፣ ዓይኑን አፍጥጦበት ፣ ሂድ ካጠገቤ አለው!  ።

ዛሬም!
አንዱ ግም ላይበቃ ፣ ሌላው ተደምሮ
ግም ለግም  ባንድ ላይ
የሚቹን በርጩማ ፣ ጠረን ተሸክሞ
ዕርመ በላ ሁሉ ፣ በጥቅም ታውሮ
ንጹህ ዓየር ሊበክል ፣ ከመሃል ተሠንቅሮ!
አሁንም ይዳዳዋል ፣ ሞቱን ተጠራጥሮ፣
እኮ!  ቁርጡ ይነገረው!
ሕዝቡም አምጾበት ፣ ባሣየው አበሣ
በርጩማማ ሞቷል ፣ዳግም ላይነሣ!።

07/29/10

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.